# እንደ ንቅሳት እየቆየ የማኅላ ባህሪይ!

**ከሃብሮማይ** (07/07/09)

ማንኛውም ህዝብ በሚኖርበት አከባቢ ሰላም የማይፈልግ አለ ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ሰላምን የሚፈልገው ደግሞ ወደ ፈለገው ቦታ በነጻነት እንዲዘዋወር፤ሰርቶ ኑሮውን እንዲገፋ፤ልጆቹ በሰላም ወጥተው በሰላም እንዲገቡለት...ወዘተ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች ፍላጎታቸው ለማሳካት ከሰላማዊና ሕገመንግስታዊ አካሄድ ወጥተው የህዝቦችን ሰላም እያናጉ በመሆናቸው ዓለም የነዚህን የህዝቦች ፍላጎት የሚያናጉና በሰላም ወጥተው እንዳይገቡ በተለያዩ ቡድኖች የተለያዩ እኩይ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ለምሳሌ አየር መንገድ ጠለፋ፤ንጹሃን ሰዎችን ማገት፤ታዋቂ ሰዎችና ዲፕሎማቶችን ማገት፤መረከቦችንም እንዲሁ ...ወዘተ

ለዚህም ነው ዓለማችን ይህን መንግስትን እያስፈራና ህዝብን እያሸበረ የመጣውን ተግባር ለማስቆም የተለያዩ ሕጎች እያወጣች የምትገኘው፡፡ በመጀመርያ ሽብርተኝነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመግለጽ ያስቸግር ነበር፡፡የተለያዩ አገሮች እንደየ አመለካከታቸው እየገለጹት ስለነበር አንድ ወጥ የሆነ አገላለጽ አልነበራቸውም ፡፡ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተወሰነ መልኩ መግባባት ያለበት ትርጓሜ እየያዘ መጥቷል፡፡ ሽብርተኝነት ማለት የፖለቲካ፤የሃይማኖት፤ወይም የርእዮተ ዓለም (ideology) ዓላማን መንግስትን በማስገደድ ወይም ህዝብን በማስፈራራት ለማራመድ በማሰብ በሰዎች ላይ የህይወት፤የአካል ጉዳት የማድረስ፤፤ ንብረት የማውደም ድርጊት ማለት ነው፡፡ይህ በመሆኑ ሽብርተኝነትን ለመከላከል የሚያሰችሉ 12 የዓለም አቀፍ ስምምነቶች አሉ፡፡እነዚህ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ሽብርተኝነትን ለመዋጋት አገራት ፤መንግስታና

ህዝቦች በትብብርና በጋራ መስራት እንዲያስችላቸው ነው የወጣው ፡፡ እነዚህን ስምምነቶች በተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ሆነ በተለያዩ አህጉራዊና አከባብያዊ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ ግንኙነት ደረጃ ትልቅ ቦታ ነው የተሰጣቸው ፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ምንም እንኳ የዓለም አቀፍ የሽብርተኝነት መከላከል ስምምነት ብንፈርም ሽብርነኝነትን በተመለከተ በግልጽ የተደነገገ የሽብርተኝነት የወንጀል ሕግ በዝርዝርና በግልጽ የሰፈረበት አልነበረም፡፡ ስለሆነም በአገሪቱ የተለያዩ የሽብር ድርጊቶች ሲፈፀሙ ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ብዙ ንፁሃን ሰዎችን ለሞት የፈረደ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል፤በትግራይ ሆቴልና በግዮን ሆቴል የተከሰተው የቦምብ ፍንዳታ ፤ በሰላም ባስ የተከሰተው የቦምብ ፍንዳታ ፤በኦጋዴን በኢትዮጵያውያንና ቻይናውያን የተፈፀመውን ግፍ የተሞላበት ግድያ ፤በታክሲዎች ላይ የተፈጸመው ፍንዳታ፤በነዳጅ ማደያ የተከሰተው የቦምብ ፍንዳታ፤ በግብፁ ፕሬዚዳንት ሁስኒ ሙባረክ በአዲስ አበባ ውስጥ የተደረገው የግድያ ሙከራ …ወዘተ ሲከሰቱ ይህን እኩይ ድርጊት የፈጸሙት ሽብርተኞች በሰሩት ጥፋት መጠን ተገቢውና ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ለመቅጣት ያለውን የወንጀል ሕግ በቂ አልነበረም፡፡ስለሆነም ይህ በአስከፊነቱ በልዩ ሁኔታ መታየት ያለበትን የሽብርተኝነት ወንጀል ለሰሩት እኩይ ስራ የሚመጣጠን የሽብርተኝነት ሕግ ያስፈልጋል፡፡

ሽብርተኝነትን በተመለከተ መንግስት ረቂቅ አዋጅ አውጥቷል፡፡ይህን አዋጅ የወጣበትን ምክንያት ከላይ እንደተገለጸው ሽበርተኝነትም በተመለከተ የወንጀል ሕግ ባለመኖሩ እንዳለ ሆኖ ይህንን ወንጀል በአገራችን በተለያዩ ጊዜያት በመከሰታቸው ከዚያም አልፎ የአፍሪካ ቀንድ የሽብርተኝነትን ተጋላጭ እየሆነ ያለውን ዕድል ሰፊ በመሆኑ (ለምሳሌ በኤርትራና በሶማልያ ያለውን ሁኔታ) ፤ ይህንን ለመከላከል ደግሞ ስለ ሽብርተኝነት አስቀድሞ መረጃ ማግኘት የሚያስችል፤ ለሕግ አስፈፃሚ አካላት ስልጣን የሚሰጥ ፤ የተጠናከረ መረጃ የማሰባሰብ ስርዓት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ

በመገኘቱና የሕግ አስከባሪ አካላት ሽብርተኝነትን በብቃት መከላከል የሚያስችላቸው ስልጣን በሕግ ለመስጠት ነው፡፡በሌላም ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የሽብርተኝነት መከላከል ስምምነቶች ፈርማለች፡፡በዓለም አቀፍ የሚደረጉ ማንኛውም ስምምነቶች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በሕገ መንግስቱ ተደንግገዋል ፡፡ስለዚህ ይህን የሽብርተኝነት ረቂቅ ሕግ መውጣቱ የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ተገዢ ለመሆን አገሪቱ በተስማማችበት መሰረት ግዴታዋን በብቃት እንድንዋጣ ም ያደርጋታል፡፡

ህዝቦችን በሰላም ወጥተው በሰላም የሚገቡበትና ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ያለ ምንም ስጋት በሰላም የሚኖርበት፤እንዲሁም የህግን ክፍተት ተጠቅመው በሽብር የሚሳተፉ፤በፋይናንስና በዕውቀት(በምክር) የሚተባበሩ፤ ሽብርን የሚያወድሱ፤ሽብርን የሚያነሳሱ ሁሉ ተጠያቂ የሚያደርግ በመሆኑ ማንኛውም የተለየ ሃሳብና አመለካከት ያለው ግለሰብ ወይም ቡድን የሚያነሳቸው ጥያቄዎችና የሚፈፅማቸው ድርጊቶች ሁሉ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲሄድ የሚያደርግ ዴሞክራሲ፤ልማትና ሰላም የሚገነባ በመሆኑ ወቅታዊ፤ትክክልና ተገቢ ነው እላለሁ፡፡

ይሁን እንጂ ይህን የወጣውን ረቂቅ ሕግ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሰፊው እየተኮነነ ነው፡፡በተለያዩ ጊዜያት ስለ ረቂቅ ሕጉ የሚሰጡት አስተያየቶች ሕጉ አስፈላጊ እንዳልሆነና ለኢትዮጵያ የሽብርተኝነት ሕግ እንደማያስፈልጋት፤ ያላትን የወንጀል ሕግ በቂ ነው ብለውናል፡፡ በመጀመርያ ደረጃ ኢትዮጵያ እንደ ሌሎች አገሮች ሁሉ በአለም አቀፍ ስምምነቶች የምትገዛ አገር ነች፡፡ከዚያም አልፎ ለአገራችን ብሎም ለአፍሪካ ቀንድ ስጋት የሆነውን የሽብር አደጋ እጁን አጣጥፋ ትቀመጥ ማለት የአገሪቱ የሉዓላዊነት ባለቤት የሆኑትን ህዝቦቿ አሳልፈህ እንደ መስጠት ነው የምቆጥረው፡፡ሽብርተኝነትን በተደጋጋሚ የተፈፀመባት አገር ይህንን ረቂቅ በመውጣቱ እሰየው ማለት ሲገባቸውና ይህን ለህዝቦቿ ደህንነትና ሰላም ትልቅ አስተዋጾ ያለውን ረቂቅ ሕግ መደገፍ ሲኖርባቸው "የሽብርተኝነት ሕግ ለኢትዮጵያ አያስፈልጋትም የወንጀል ሕጉን

ይበቃታል" ማለታቸው ሽብርተኞች ባለው የወንጀል ሕግ መቀጣት አለባቸው የሚል እንደምታ ያለውና ሆን ብሎ (intentionally) በፖለቲካዊ ፤ ሃይማኖታዊ አመለካከት ህዝብንና መንግስትን ለማሸበር ሰው የገደለና በአጋጣሚ ሰው የገደለ እኩል የሆነ ፍርድ ማግኘት አለበት ማለታቸው ነው፡፡ይህ ደግሞ በሌላ አገላለፅ ሽብርተኝነትን መደገፍ ሆኖ ነው የሚሰማኝ፡፡

በአገራችን የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ይህ ብቻ አይደለም የተባለው፡፡እሱ ብቻ ቢሆንማ የግንዛቤ ችግር ስላላቸው ይሆናል ብዬ ሽብር ለመፍጠር የሚፈፀሙ ወንጀሎችና ሌሎች ወንጀሎች ያላቸውን ልዩነት ባስነበብኳቹ ነበር፡፡ይሁን እንጂ ተቃዋሚዎች ስለ ረቂቅ ሕጉ ያላቸው አመለካከት ከዚህ ባለፈ መልኩ የሽብርተኝነት ረቂቅ ሕግ ራሱ "ሽብር"እንደሆነ ገልፀውልናል፡፡እኔም በጣም የገረመኝ ነገር ይሄ ነው፡፡ረቂቁ የኢትዮጵያ ፍፁም ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ዕድገት ማየት የማይፈልጉ አሸባሪዎችን ቦታቦታቸው የሚያስገባና ህዝባችን ያለ ምንም ስጋት እንዲኖር የሚያደርግ ሕግ እያለ ለምንድነው "ሽብር"ያሉት ብዬ ለራሴ መጠየቅ ጀመርኩ፡፡

ተቃዋሚዎች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ሕገ ወጥና ሕጋዊ አካሄድን እያጣቀሱ መምጣታቸው የማይካድ ሐቅ ነው፡፡ለምሳሌ በ1997 ዓ/ም ከምርጫ ጋር ተያይዞ በህዝብ ያጡትን ድምፅ ተስፋ አስቆርጧቸው ህገ መንግስቱ በሃይል ለመናድ መንቀሳቀሳቸው ይታወሳል፡፡እዚህ ላይ ተቃዋሚዎች ሁለት አማራጮችን ይዘው የሰልጣን ጥማታቸውን ለማርካት ተንቀሳቅሰዋል፡፡ከተሳካ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ካልተሳካ ደግሞ በሃይል መንግስትን መጣል! ነገር ግን የሕግ የበላይነትን ስላሸነፈ ያሰቡትን ነገር ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡

እነዚህ ሰዎች ካለፈው ስህተታችን ተምረናል ብለው ለመንግስትና ለህዝብ ይቅርታ ጠይቀው ነው ወደ ፖለቲካ መድረኩ የተቀላቀሉት፡፡ይሁን እንጂ

ይዘውት ያሉት ዓላማ ከሕጋዊና ሰላማዊ ትግል ጋር አልጣጣም ብሏቸው ነው መሰለኝ ትናንት እንደነበሩ አሁንም አሉ፡፡ምክንያቱም ተቃዋሚ ፓርዎች የአገራችን ክብር የሚያስጠብቁ፤ ሰላማዊ ትግልን የሚያበረታቱና የፖለቲካ ምህዳሩ የሚያሰፉ ሕጎች ሲወጡ ሙሉ በሙሉ ማውገዝ መለያቸው ሆነዋል፡፡የበጎ አድራጎት ድርጅት ሕግ፤የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕግ፤የፕረስ ሕግ፤የምርጫ ቦርድ ሕግ …ወዘተ አብዛኛዎቹ ሲተቹት ይታያሉ፡፡ሕግ በወጣ ቁጥር የሕግ ፍራቻ (law phobia) ያላቸው ይመስል ሕግ በወጣ ቁጥር ስራቸው መቃወም ብቻ ሆነዋል፡፡ስልጣን ከያዙ አገሪቷ ያለ ሕግና ስርዓት ለማስተዳደር አናርኪዝምን የሚያቀነቅኑ ነው የሚመስሉት፡፡

ባህሪያቸው ሁሉ እንዲህ ስለሆነ ነው አሁንም የፀረ ሽብርተኝነትን ረቂቅ አዋጅ እየተቃወሙት ያሉ፡፡ከላይ የገለጽኳቸውን ሕጎች ሲወጡ የፖለቲካ መድረኩ “ጠቧል” እያሉ ነበር አሁን ደግሞ ይህ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ሲረቀቅ የፖለቲካ መድረኩ “ተዳፍኗል” እያሉን ነው፡፡ በ ፖለቲካ መድረክ መስፋትና መጥበብ ብዙ መፃሕፍቶች በመፃፍ የሚታወቀው ጀርመናዊ ፍላስፋ ጀርገን ሃበር ማስ ሲገልፅ “ፖለቲካዊ ምህዳር (political sphere) ሰፍተዋል የሚባለው ህዝብን በብዛት ባሳተፈ መልኩ ባለው ተጨባጭ ሕግ (existing law) የሚደረግ ጨዋታ ነው” ይላል፡፡ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ የፖለቲካ ምህዳር ሰፊ የሚባለው ፓርቲዎች እንደፈለጉ ያለ ሕግና ስርዓት ሲንቀሳቀሱ ነው የሚል አገላለፅ ያላቸው ይመስላል ፡ ፡

ለዚህም ነው ተቃዋሚዎች ሕግ በወጣ ቁጥር የፖለቲካ ምህዳሩን ጠቧል ብለው የሚደስኩርልን ያሉት፡ ፡ያለ ሕግና ስርዓት እንዳሻቸው መፈንጨት የሚፈልጉ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች በአገራችን የተፈፀሙትና የብዙ ንፁሃን ህይወት የቀጠፈ የሽብር ተግባር መኖሩ እያወቁ በአገራችን ሽብር የሚባል ነገር የለም ተራ ወንጀል ብቻ ነው ያለው ስለሆነም ኢትዮጵያ ይህን የሽብርተኝነት ሕግ አያስፈልጋትም ሌሎች አገሮች ግን ያስፈልጋቸዋል ነው እያሉን ያሉት፡ ፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው

ይህ አዋጅ የወጣበትን ምክንያት አገሪቱ የሽብር ሰለባ እየሆነች በመምጣቷ፤ የአፍሪካ ህብረትና የተባበሩት የመንግስታት ድርጅት በሽብርተኝነት ጉዳይ ላይ ያፀደቁት ኮንቬንሽኖች የኢትዮጵያ አካል መሆን ስላለባቸውና የዓለም አቀፍ ግዴታም ስላለባት ነው ፡ ፡ ተቃዋሚዎች ግን ለምንድነው ለኢትዮጵያ የሽብር ሕግ አያስፈልጋትም ያሉት? እርግጥ ነው ይህ የፀረ ሽብር አዋጅ ለአሸባሪዎች ሽብር እንደሚፈጥርላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው ፡ ፡ ለሕጋዊና ሰላማዊ ዜጋና ቡድን ግን ረቂቅ አዋጁ የህይወቱ ዋስትናና ከለላ ነው ፡ ፡

ሽብርተኝነት የንፁሃን ህይወት በጅምላ የሚያጠፋ ፤ አካልን የሚያጎድል ፤ የሃገርን ሃብት የልማት አውታሮችና ተቋማትን የሚያወድም ሃላፊነት የጎደለው ተግባር በመሆኑ ሁሉም ተቃዋሚዎች ማውገዝ ሲገባቸው እንዲህ በደፈና ረቂቅ ሕጉ መቃወማቸው ያላቸውን የተደበቀ ባህሪይ ቀስ በቀስ እንደ ንቅሳት እየጎላ መምጣቱ ያሳያል ፡ ፡ በመጨረሻም የሽብርተኝነት ተግባር በጣም ከባድና ውስብስብ በመሆኑ ለዚህ ውስብስብ ያለ እኩይ ተግባር ለመከላከል ረቀቅ ያለ ሕግ መርቀቁ ተገቢና ትክክል ነው ፡ ፡ ሕግ ሆኖ ቢወጣ ለአገራችን ሰላም ፤ልማትና ዴሞክራሲ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል እላለሁ ፡ ፡ ሰላም!